# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| 1ki Diro Kiiro 2<br>Hawaasa, Ella 27, 2012 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፪<br>ሀዋሳ፣ ሰኔ ፳፯ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም |
|---|---|---|



**Amado**

**Lallawu Kiiro 2/2012**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Affini Gaazeexa Xintate Fulino Lallawa …………… Qoola ….**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፪/፳፻፲፪**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ……….. ገጽ…**


## Lallawu Kiiro 2/2012

## Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Affini Gaazeexa Xintate Fulino Lallawa

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimmanni fulanno seera lallambanni gazeexa xinta hasiisinota ammanatenni;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bayriidi Seera quwa 48 cinaancho quwa (3) fidale (a) garinni konninni aane nooha lallamboonni.

## አዋጅ ቁጥር ፪/፳፻፲፪

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕጎች የሚታተሙበት ጋዜጣ ማቋቋም አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፤

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ያለው ታውጇል፡፡


**Mittu Waagi ….**
*ያንዱ ዋጋ*

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

**1. Harancho Umo**

Konne Lallawa **“Affini Gaazeexa Xintate Fulino Lallawa Kiiro 2/2012”** yine xawisa dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro aanno gede assa hooguro konni lallawi giddo:

1. **“Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
2. **“Amaalete Mine”** yaa Qoqqowi deerrinni aliidi biilloonyi noosihonna seera fushshanno bisooti.
3. **“Jeefisiisaanote Amaale Mine”** yaa Qoqqowoho aliidi seera jeefisiisanno bisooti.
4. **“Lallawa”** yaa qoqqowu amaale mininni fulanno seera ikke jeefisiisaanote bisi e’annonna amaalete mininni kaajjanno sheemateno hanqafanno.
5. **“Wodho”** yaa qoqqowu amaale mininni fulanno lallawa woy wole hajo loosu aana hosiisate qoqqowu jeefisiisaanote amaale mininni fulanno seerati.
6. **“Biddissa”** yaa qoqqowu amaale mininni fulanno lallawa woy jeefisiisaanote amaale mininni fultanno wodho loosu aana hosiisate hajo la’’anno loosu mini fushshanno

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ **“አፍኒ ጋዜጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪/፳፻፲፪”** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡

፪. **“ምክር ቤት”** ማለት በክልል ደረጃ ከፍተኛ ስልጣን ያለውና ሕግ የሚያወጣ አካል ነው፡፡

፫. **“የመስተዳድር ምክር ቤት”** ማለት በክልሉ ከፍተኛ ሕግ አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

፬. **“አዋጅ”** ማለት በክልሉ ምክር ቤት የሚወጣ ሕግ ሆኖ በሥራ አስፈጻሚ የተደረገና በምክር ቤቱ የሚጸድቅ ስምምነትንም ያጠቃልላል፡፡

፭. **“ደንብ”** ማለት በክልል ምክር ቤት የወጣ አዋጅን ወይም ሌላ ጉዳይን ለማስፈጸም በመስተዳድር ምክር ቤት የሚወጣ ሕግ ነው፡፡

፮. **“መመሪያ”** ማለት በክልሉ ምክር ቤት የወጣ አዋጅን ወይም በመስተዳድር ምክር ቤት የወጣ ደንብ ለማስፈጸም በሚመለከተው መስሪያ ቤት የሚወጣ ዝርዝር ሕግ ነው፡፡

tittirshu seeraati.

7. **“Hajo La’annosi Loosu Mini”** yaa lallawunni woy/nna wodhotenni worroonni hajubba loosu aana hosiisate woy/nna loosu aana hosanno gede assate roorreenya uynoonni woy gadacho noose biiro, biilloonye, komishiine, ejense, borrote mine woy wole taalcho bisooti.

**3. Xintama**

“Affini Gazeexa” yine woshshinanni Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaale Mini allaalshi hundaanni fulanno seeru gaazeexi konni lallawinni xintamino.

**4. Lallambanni Hajubbanna Wo’ma Hasiissanno Ikkituwa**

1. Amaalete Mininni fulanno lallawi hattono qoqqowu mootimma e’annonna amaalete mini kaajjishshanno sheemaati, jeefisiisaanote amaale mininni fultanno wodhonna hajo la’annosi loosu mininni fulanno biddissi attamanniha ikkanno.

2. Amaalete Mini, Jeefisiisaanonna Yooaate bisubba hattono aye kalaqamu manchi woy seerunni mannimmate afamooshshe afi’rino bisi Affini Gaazeexira lallamboonni seerubba loosu aana hosiisate gadadi heerannosi.

3. Affini Gaazeexi attamamannohu Sidaamu,

፯. **“የሚመለከተው መስሪያ ቤት” ማለት** በአዋጁ እና/ወይም ደንቡ የተደነገጉ ጉዳዮችን ለመፈጸም እና/ወይም ለማስፈጸም ስልጣን የተሰጠው ወይም ግዴታ የተጣለበት ቢሮ፣ ባለስልጣን፣ ኮሚሽን፣ ኤጀንሲ፣ ጽህፈት ቤት ወይም ሌላ ተመሳሳይ አካል ነው፡፡

**፫. ስለመቋቋም**

“አፍኒ ጋዜጣ” ተብሎ የሚጠራ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የሕግ ጋዜጣ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**፬. የሚታተሙ ጉዳዮችና መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

፩ በክልሉ መንግሥት የሚደረግና በክልሉ ምክር ቤት የሚጸድቅ ስምምነትን ጨምሮ በሕግ አውጪው የሚወጣ አዋጅ፣ በመስተዳድር ምክር ቤት የሚወጣ ደንብ እና በሚመለከተው መስሪያ ቤት የሚወጣ መመሪያ የሚታተም ይሆናል፡፡

፪ ምክር ቤት፣ ሕግ አስፈጻሚ እና ሕግ ተርጓሚው አካል እንዲሁም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው በአፍኒ ጋዜጣ ላይ የወጡ ሕጎችን ስራ ላይ የማዋል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፫ አፍኒ ጋዜጣ የሚታተመው በሲዳሙ አፎ፣

Amaarunna Ingilizete Afuubbannii ikkanno.

**5. Affini Gaazeexa Attamisiisate Biilloonyi**

Qoqqowu Amaalete Mini Affini Gazeexa attamisiisate looso massagganno.

**6. Jeefishshu Noo Hinkiilo**

Konni gaazeexi aana lallawantanno seerubba Sidaamu Afiinna wolu afii hinkiilo mereero kipheenyu heeranno yannara Sidaamu Afii hinkiilo jeefishshu heerannose.

**7. Lallawu Loosu Aana Hosanno Yanna**

Kuni lallawi Ella 27/2012 M.D. hanafe loosu aana hosanno.

**Hawaasa, Ella 27, 2012 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ይሆናል።

**፭. አፍኒ ጋዜጣን የማሳተም ስልጣን**

የክልሉ ምክር ቤት የአፍኒ ጋዜጣ ሕትመት ስራን ያደራጃል።

**፮. ተፈጻሚነት ስላለው ቅጂ**

በዚህ ጋዜጣ ላይ የሚታተሙ ሕጎች የሲዳሙ አፎ እና ሌላ ቋንቋ ቅጂ መካከል ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ የሲዳሙ አፎ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**፯. አዋጁ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፯ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል።

**ሀዋሳ፤ ሰኔ ፳፯ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**